# ኢትዮጵያ በተ.መ.ድ ፀጥታው ም/ቤት ተለዋጭ አባል መሆኗ መመረጥ ስላለው ፋይዳ፤

ነጋ ካሳ 12-20-16

እ.ኤ.አ 1945 የሁለተኛ አለም ጦርነት ማብቃቱን ተከትሎ የተቋቋመው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከሚፈፅማቸው ተግባራት መካከል የአለምን ሠላም፣ፀጥታና የደኅንነት ማስጠበቅ፣የድህነት ቅነሳና ዘላቂ የልማት ግቦችን ማስፈፀም፣ሰብአዊ መብቶች እንዲጠበቁ ማድረግ፣አለምአቀፍ ህጎችን ማስከበርና ሰብአዊ እርዳታዎች ማቅረብ የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው::በመሆኑም የዚህ ፅሁፍ ዋና ትኩረት የሚያደርገው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስልጣናን አካላት ዋነኛ በሆነው የፀጥታው ምክር ቤት ላይ ብቻ ነው:: የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ዋነኛ የሥልጣን አካል ሲሆን የአለምን ወሳኝ ሠላም፣ፀጥታና የደኅንነት ጉዳዮችን የሚከታተል አካል ሆኖ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር 7 መሰረት በአለም ላይ የሚነሱ ግጭቶችና አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ እልባት እንዲያገኙ የመፍትሄ ሀሳቦችንና የማግባቢያ አማራጮችን የሚያቀርብ ፤እነዚህ የሰላም መፍትሄዎችና አማራጮች የማይሰሩ ሆነው ከተገኙ በአንድ ሉዓላዊ ሀገር ላይ ከኢኮኖሚ ማዕቀብ እስከ ጦርነት ማወጅ የሚደርስ እርምጃ የሚወስድ ነው:: በተጨማሪም በአንድ ሀገር ውስጥ ወይም በሁለቱ ሀገሮች መካከል የተፈጠረ ግጭት የውጭ ሰላም አስከባሪ ኃይል ማሰማራት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሰላም አስከባሪ ኃይል እንዲሰማራ የመወሰንና የማሰማራት ስልጣን አለው:: ይህ የሥልጣን አካል ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት ያላቸው አምስት የዓለማችን ኃያል አገሮች (አሜሪካ፣ ሩሲያ፣ ቻይና፣ ታላቋ ብሪታንያና ፈረንሳይ) ቋሚና ሌሎች አሥር ተለዋጭ አባላት አሉት፡፡የእነዚህ የአሥሩ ተለዋጭ አባላት በም/ቤቱ ያላቸው የስራ ዘመን ሁለት አመት ብቻ ነው::በም/ቤቱ አሥር ተለዋጭ አባላት ምርጫ በየሁለት አመት በአዳዲስ አስር ተለዋጭ አባላት መተካት በአሰራር ላይ ክፍተት የሚፈጥር መሆኑ ስለታመነበት በየአመቱ አምስት ተለዋጭ አባላት ምርጫ ከየአህጉራት እንደኮታቸው መጠን በየተራ ይመረጣሉ::

ከፀጥታው ምክር ቤት አሥር ተለዋጭ አባላት ውስጥ ሦስቱ ከአፍሪካ ናቸው፡፡በአሁኑ ሰዓት አንጎላ፣ሴኔጋልና ግብፅ አፍሪካን ወክለው በም/ቤቱ ያሉ ሲሆን ከፊታችን ጥር የአባልነት ዘመኗን በማጠናቀቅ የምትሰናበተው አንጎላ በኢትዮጵያ ትተካለች::

ኢትዮጵያ ሰኔ 21 ቀን 2008 ዓ.ም. በኒውዮርክ ተካሂዶ በነበረው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባላት ምርጫ ድምፃቸውን ከሰጡ 190 አገሮች መካከል የ185ቱን ድጋፍ በማግኘት አባል ሆና መመረጧ ይታወሳል:: ምንም

እንኳን ኢትዮጵያ የቀድሞ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ የአሁኑ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መስራች አባል ብትሆንም በፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል ሆና የሰራችው ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ ነበር::ይህም እ.ኤ.አ. ከ1967 እስከ 1968 እንዲሁም ከ1989 እስከ 1990 ናቸው:: የዘንድሮ ምርጫዋ ለሶስተኛ ጊዜ መሆኑ ነው:: ይህ ተሳትፎዋ ከ1950ዎቹ አንስቶ እየጎላ ለመጣው አካባቢያዊና ዓለማቀፍ ሰላምና ፀጥታ የማረጋገጥ ሚናዋ አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ ተብሎ የሚወሰድ ነው:: በዚህ አካባቢያዊና ዓለምአቀፍ ሰላምና ፀጥታ የማረጋገጥ ተሳትፎዋ በኮሪያ ፣በኮንጎ ፣በሩዋንዳ፣ በብሩንዲና በላይቤሪያ በሰላም ማስከበር ውጤታማ ተልዕኮ የፈፀመች ስትሆን በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በሶማሊያ፣ በሱዳንና በደቡብ ሱዳን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ ጠንካራ ተሳትፎ እያደረገች ትገኛለች፡፡

ለመሆኑ ኢትዮጵያ የፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል መሆኗ ምን ፋይዳ አለው?

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰላም አስከባሪ ጦር በማዋጣት በዓለም 2ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ኢትዮጵያ ብጥብጥና ጦርነት መለያ በሆነው በአፍሪካ ቀንድ የውስጥ ሠላሟን አስጠብቃ ለሌሎች የጎረቤት ሀገራት ሠላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የምትተጋ ሀገር ሆናለች:: ኢትዮጵያ በጎረቤት ሀገሮች ሰላም እጦት የሚጎርፉ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ስደተኞች በማስተናገድም ያላት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡በመሆኑም ኢትዮጵያ በታሪኳ ለ3ኛ ጊዜ የጸጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል ሆና በመመረጧ እነዚህን ሚናዎቿንና የአፍሪካን ጥቅሞች ለማስጠበቅ የምታደርገውን እንቅስቃሴ አጠናክራ እንድትቀጥል ይረዳታል::

**ኢትዮጵያ** በምክር ቤቱ ሰላምና ጸጥታን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሲተላለፉ ሃሳብ በማቅረብና ውሳኔ በማሳለፍ ከኃያላን አገራት ጋር አብሮ መስራትና መደራደር ያስችላታል፡፡በዚህ ረገድ በተለይ የሶማሊያ፣ የደቡብ ሱዳን ብሎም ሌሎች የአፍሪካ ማለትም የማሊ፣የናይጄሪያ፣የሊቢያ፣የዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣የቡርንዲ ሰላምና ጸጥታ ጉዳዮች በም/ቤቱ በቂ ትኩረት አግኝተው ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ የተለያዩ የሰላም አማራጮችን በማቅረብ ሚናዋን እንድትወጣ ይረዳታል:: ለአንድ አገር ዕድገትና ልማት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ያለው ሰላም በጎረቤት ሀገሮች ፣በአፍሪካ ብሎም በአለም እንዲሰፍን ኢትዮጵያ በተግባር ያደረገችውና እያደረገች ያለው ጥረት የተመድ የፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል ሆና እንድትመረጥ ያስቻላት በመሆኑ ከምንም በላይ በም/ቤት ቆይታም ጊዜ ከአለም ሰላም በላይ ሌላ አጀንዳ ሊኖራት አይችልም፡፡በመሆኑም ይህን ሰላም ዘብነቷን ለአለም ማህበረሰብ በቅርበት

ለማስረዳት በአሁኑ ሰዓት ከጸጥታው ምክር ቤት የተሻለ ቦታ ሊኖር ስለማይችል እድሉን ለመጠቀም ያስችላታል::

ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ ላይ ተጽእኖ ለማድረግ የሚፈልጉ አካላትን ለመከላከልም ጥሩ ዕድል ይፈጥርላታል። ኢትዮጵያ በጎ የሚመኙ በርካታ ወዳጅና ደጋፊ ሀገራት ያሏትን ያህል ለኢትዮጵያ እድገትና ሰላም እንቅልፍ የሚነሳቸው ጥቂት ሀገሮች መኖራቸው እሙን ነው:: የእነዚህ ጥቂት ለኢትዮጵያ በጎ የማይመኙ ሀገራት ስውርና ገሃድ ሴራዎቻቸውን በቅርበት በመከታተል በሀገራችን ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመቀነስና ከተቻለም ለማስቆም **በጸጥታው ምክር ቤት** አባል መሆን ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው::

ሌላው ፋይዳ ኢትዮጵያ የአፍሪካውያንና የሦስተኛው ዓለም አገራትን ድምጽ ለማሰማትም ይረዳታል። በምክር ቤቱ ውስጥ የአፍሪካን ድምፅ ከማሰማትም ባሻገር በአህጉሪቱ ላይ የሚተላለፉ አሉታዊ ውሳኔዎች እንዳይፀድቁ ጥብቅና ለመቆም ያግዛታል። በተለይ በምሥራቅ አፍሪካ የሚታየውን የሰላምና ጸጥታ ችግር ለመፍታት የጀመረችውን ጥረት በማጠናከር ብሎም የራሷን ሰላም በማስቀጠል ረገድም ተጨማሪ አቅም ይፈጥርላታል።

በድርቅና በድህነት የሚታወቀውን የአገሪቷን የቀደመ ገጽታ ለመቀየር የሚኖረው ፋይዳም ቀላል አይሆንም። መድረኩን የገፅታ ግንባታ በማድረግ የዓለም አገራት በኢኮኖሚም ሆነ በሌላ መስክ ከአገሪቱ ጋር ተባብሮ ለመስራት ፈልገዋት እንዲመጡ በር ይከፍትላታል። ኢትዮጵያ ለዚህ ድል የበቃችው ባላት ሰላምና ለሌሎች አገሮች ሰላም መረጋገጥ ባበረከተችው አስተዋጽኦና በከፈለችው መስዋዕትነት ነው። ከምንም በላይ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፍ የተመዘገበው ከፍተኛ እድገትም የተጫወተው ሚና ቀላል አይደለም። ከዚህ ሁሉ ድል በስተጀርባ ደግሞ ውጤታማው የአገሪቷ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ትልቁን ቦታ ይይዛል::

በፖለቲካው መስክ የሚኖረው ተጠቃሚነት አሁን ያለው የአገሪቷ ተደማጭነትና ተጽዕኖ ፈጣሪነቷ ከአፍሪካ አልፎ በዓለም ደረጃ እንዲያድግ እድል ስለሚሰጥ ዲፕሎማሲዋን በማስፋት ከጸጥታው ምክር ቤት አባላት ልምድ ለመውሰድም ያስችላታል:: በአፍሪካ ያለውን አለመረጋጋት እንዲፈታ ለማድረግ፣ ሽብርተኝነትን ከሌሎች አገሮች ጋር በመሆን ለመዋጋት **እንዲሁም** ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በሚገታበት ሁኔታ ዙሪያ ከኃያላን አገራት ጋር በመካከር የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ ይረዳታል::**ከሁሉ በላይ ግጭትና ጦርነት በማልተለየው የምስራቅ አፍሪካ በተለይ ቀይ በባህሩንና አከባቢውን ለመቆጣጠር በሚል በመካከለኛ ምስራቅ አንዳንድ ሀገራትና በሌሎች መካከል እየተደረገ ያለው ፉክክር ከሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም ጋር የሚኖረውን አሉታዊ ተፅኢኖ በጥናት በመፈተሽ መፍትሄ ማበጀት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው በኤርትራ የጦር ሰፈሮቻቸውን በመገንባት ላይ ያሉ ሳውዲ አረቢያ፣የተባበሩት አረብ ኤምሬቶችና ኳታር ሲሆኑ በተመሳሳይ ግብፅም የራሷን የጦር ሰፈር ለማቋቋም የኤርትራ ባለስጣናትን ይሁንታ ማግኘቷ እየተነገረ ይገኛል::በተመሳሳይ**

በጂቡቲ ሳውዲአረቢያና ኳታር፣በሶማሊያ ላንድ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እንዲሁም በሶማሊያ ቱርክ ተጨማሪ የጦር ሰፈሮቻቸውን ለማቋቋም በሂደት ላይ ይገኛሉ:: የእነዚህ ሀገሮች እንቅስቃሴ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም የሚፃረሩ ከመሆኑ አልፎ ወትሮም ግጭትና ጦርነት መለያ ለሆነው የቀጠና ሀገሮች ትልቅ የሰላም እንቅፋት መሆናቸውን ኢትዮጵያ በም/ቤቱ ከምንም ነገር በላይ ተቃውሞዋን በማሰማት የአለም ማህበረሰብ በቀጠናው ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ለማስፈን መፍትሄ እንዲያፈላልጉ ለማድረግ ያስችላታል::

ከኢኮኖሚ አንፃርም አገሪቷ በአሁኑ ወቅት የራሷን ሰላም አረጋግጣ ለሌሎችም ሰላም መስፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገች መሆኑንና የውጭ ሀገር ባለሀብቶች ባላት ሰላም ተማምነው ኢትዮጵያን ተመራጭ የኢንቨስትመንት ተደራሽ እያደረጋት መሆኑን በሚገባ በማሳየት ተጨማሪ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ወደ ሀገሪቱ እንዲሳቡ ዕድል የሚፈጥርላት ይሆናል::

የተባበሩት መንግሥታት ሲመሰረት የነበረው ነባራዊ ሁኔታ አሁን ካለው ጋር በፍጹም የማይገናኝና የተለየ በመሆኑ የጸጥታው ምክር ቤት ድምጽን በድምጽ የመሻር መቀመጫ ያላቸው አገሮች ቁጥር ከፍ እንዲል ኢትዮጵያ ከሌሎች ጋር በመሆን ጥያቄ እንድታቀርብና እንድትታገል ይረዳታል። አሁን ባለው ሁኔታ በአጭር ጊዜ ይሆናል ተብሎ ባይጠበቅም ኢትዮጵያና ሌሎች አገሮች ጥናት በማድረግ ሃሳብ በማቅረብ መታገል የሚችሉበትን አጋጣሚን ስለሚሰጥ በጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ ለማግኘት የሚያስችሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከአሁኑኑ ለመፍጠር ኢትዮጵያ በም/ቤት ቆይታዋ ሊታወሱና ሊረሱ የማይችሉ ተግባራትን ለማስመዝገብ በቂ ዝግጅት እንድታደርግ ከፍተኛ ፋይዳ ይሰጣታል:: የአሁኑን የአለም ቁመና ከግምት ያስገባ የፀጥታ ም/ቤት መዋቅራዊ ለውጥ **እንደሚያስፈልገው ምንም ጥርጥር የለውም**:: በዓለም ላይ በኢኮኖሚያቸው ጠንካራ የነበሩ አገራት እየቀነሱ መሄድ ወይም በአሉበት መቆም፣ አዳዲስ አገራትም በኢኮኖሚና በመከላከያ ጡንቻቸው እየጠነከረ መጥተዋል። በመሆኑም በምክር ቤቱ ውስጥ ተጨማሪ ቋሚ መቀመጫ የሚኖራቸውን አገራት መቀበል የግድ ይላል።የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካን ጥቅሞች በሚያስጠብቅ መልኩ እንዲዋቀር ለማድረግም ጠንክሮ መስራትን ይጠይቃል። ኢትዮጵያም ከአሁኑኑ ለዚህ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባታል።

ኢትዮጵያ በውስጥና በጎረቤቶቿ በሰራችው በጎ ሥራ ምክንያት በዓለም አገራት ዘንድ ፅኑ እምነት ማሳደር መቻሏ የፀጥታው ም/ቤት ተለዋጭ አባል ሆና በከፍተኛ ውጤት እንድትመረጥ አድርጓታል:: በአፍሪካ ወንድሞቻችንም ሆነ በዓለም ሕዝብ የተጣለባት ኃላፊነት ከፍተኛ ነው፡፡ የአፍሪካ ጥቅሞች እንዲጎሉ ማድረግ፣ በዓለም ዙርያ ሰላም እንዲሰፍን የሚመለከታቸው አካላት መፍትሔ እንዲያመጡ ፣ጥልቅና በጥናት ላይ የተመሰረተ ውይይት እንዲደረግ፣ ከዚያም ሲያልፍ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አገሮች ሰላም አስከባሪ እንዲሰማራ በማድረግ ከዓለም ሕዝብ ጋር ሆና መስራት ይጠብቅባታል፡፡ በመሆኑም በአለም መድረክ እየተገነባ ያለው ኢትዮጵያ መልካም ገፅታ የበለጠ እንዲጎላ ለማድረግም አሁንም የውስጥ ችግሮችን እየፈቱ

መሄድ፣ የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ዲፕሎማሲውን አጠናክሮ መሄድ ያስፈልጋል።

**ከአዘጋጁ፡- ጽሑፉ የጸሐፊውን አመለካከት ብቻ የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣ ጸሐፊውን በኢሜይል** nega.ktmk@yahoo.com

**ማግኘት ይቻላል::**